

# MEDICAID WORKS

## የVIRGINIA MEDICAID የሥራ ማበረታቻ ፕሮግራም ለአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች

***MEDICAID WORKS*** በVirginia Medicaid በቅጥር ላይ ያሉ ወይም መቀጠር ለሚፈልጉ የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የቀረበ የሥራ ማበረታቻ ዕድል ነው። ***MEDICAID WORKS*** ያልተቋረጠ የMedicaid ሽፋን እንደያዙ፣ የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰራተኞች ከፍ ያለ ገቢ እንዲያገኙ እና የበለጠ ቁጠባ ወይም ሃብቶችን እንዲይዙ የሚያስችል የMedicaid ዕቅድ ነው። ይህ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ዕቅድ ተሳታፊዎች እስከ $75,000 እንዲያገኙ እና ከገቢያቸው እስከ $45,976 (ከጃንዋሪ 1፣ 2024 ጀምሮ) እንዲቆጥቡ ያስችላል።

***MEDICAID WORKS*** ጠቅላላ ተቆጣሪ በወር ለግለሰብ ከ$1,732፣ ወይም ለጥንዶች ደግሞ ከ$2,351 ያልበለጠ ገቢ፣ እንዲሁም ለግለሰብ ከ$2000 (ለጥንዶች $3000) ያልበለጠ ሃብት ላላቸው፣ የአካል ጉዳት ላለባቸው እና አይነ ሥውር ለሆኑ ነባር እና አዲስ የMedicaid ተሳታፊዎች ይገኛል።

ለዚህ የሥራ ማበረታቻ የብቁነት መስፈርቶቹን የሚያሟሉ የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች፣ የሚከተሉትን ካሟሉ በ***MEDICAID WORKS*** ውስጥ ለመሳተፍ ሊመርጡ ይችላሉ፦

- ✓ የ***MEDICAID WORKS*** ስምምነትን ይሙሉ፤
- ✓ ተቀጥረው ወይም ሥራ የሚጀመርበትን ቀን የሚያረጋግጥ ሰነድ ከአሰሪው የተገኘ;
- ✓ ዕድሜያቸው ቢያንስ 16 ዓመት እና ከ 65 ዓመት በታች የሆኑ፤
- ✓ የሚገኝ ገቢን ለማስቀመጥ "የሥራ ማበረታቻ" (WIN) ሂሳብ (መደበኛ የቁጠባ ወይም ተንቀሳቃሽ ሂሳብ) በባንክ ወይም በፋይናንስ ተቋም ውስጥ መፍጠር፤ ይኸም እንደ አስፈላጊነቱ ጥቅም ላይ ይውላል፣ እንዲሁም የፋይናንስ ሃብቶችን በሥርዓት ለማስቀመጥና Medicaid ብቁ ሆነው እንዲቆዩ ያገለግላል።

ለ***MEDICAID WORKS***ለማመልከት፣ እርስዎ በሚኖሩበት ከተማ ወይም ካውንቲ ውስጥ ያለውን አካባቢያዊ የማሕበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ያነጋግሩ።

ይህ ተቋም፣ በፕሮግራሞቹ እና በአገልግሎቶቹ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በትውልድ አገር፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ ወይም በአካል ጉዳት ላይ በመመስረት ልዩነት አያደርግም።

ሜዲኬይድ ስራዎች የቨርጂኒያ ኮመንዌልዝ ፕሮግራም ነው።

*MedWorks Flyer 0124 AM*

CardinalCare Virginia's Medicaid Program

VIRGINIA'S MEDICAID PROGRAM DMAS